# አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈጽሟቸው ተግባሮች በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ያለ አላፊነት*

በንጋቱ ተስፋዬ**

## ጠቅላላ

በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 2027 መሠረት አንድ ሰው ሦስት ዓይነት አላፊነት ሊመጣበት ይችላል። አንደኛ፣ አንድ ሰው በራሱ ጥፋት[1] በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ አላፊ ይሆናል። ሁለተኛ፣ ህጉ የሚያዝ ሲሆን፣ አንድ ሰው "የሚያከናውነው ሥራ"[2] ወይም በጠባቂነት ወይም በባለሀብትነት የያዘው "ንብረት"[3] በሌሎች ላይ ላደረሰው ጉዳት አላፊ ይሆናል። በመጨረሻም፣ አንድ ሌላ ሰው በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ወይም ህጉ በሚያዘው ሁኔታ አላፊነት ሲመጣበት ለዚህ ለመጣው አላፊነት ሕጉ አላፊ ትሆናለህ ሲለው አላፊ ይሆናል።

የመጀመሪያው ዓይነት አላፊነት፣ ማለትም በራስ ጥፋት ላይ የተመሠረተው አላፊነት፣ የሁሉም አገሮች መሠረታዊ የሆነ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያትም የፍትሐብሄር አላፊነት እንዲኖር ጥፋት /ወይም የበደል ተግባር/የተፈፀመ መሆን አለበት የሚለው አስተሳሰብ ከማናቸውም ኅብረተሰብ የፍትሕ ስሜት ጋራ የሚጣጣም ሆኖ ስለሚገኝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ፀሐፊዎች ሁለተኛውን ዓይነት አላፊነት፣ ማለትም ያለጥፋት አላፊ መሆንን፣ እንደ ማህበራዊ የፍትሕ መጓደል አድርገው ይመለከቱታል። "ይህ ዓይነት የፍትሐብሄር

* ይህ ጽሁፍ በ1980 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በዚያው ዓመት ለወቅቱ የመጽሄቱ አዘጋጆች ተሰጥቶ የነበረ ነው።

** ረዳት ፕሮፌሰር፣ ህግ ፋኩልቲ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

አላፊነት በወንጀል ጉዳይ በአንድ ንፁሕ ሰው ላይ ከሚሰጥ የቅጣት ፍርድ ጋራ ተመሳሳይ ነው"[4] በማለት ይነቅፉታል።

በልዩ ሁኔታዎች ያለጥፋት አላፊነት እንዲኖር በሚደገፉትና ይህን ዓይነቱን አላፊነት ፊፅሞ በሚቃወሙት መካከል ያለው ልዩነት የሚመነጨው ሁለቱ ወገኖች ውል ሳይኖር ለሚደርሰው አላፊነት ህግ ካላቸው አመለካከት ይመስላል። ያለጥፋት አላፊ መሆንን ፊፅሞ በሚቃወሙት ሰዎች አመለካከት የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ዋነኛ ተግባር ቁጥጥር ማድረግ፣ ማለትም በደል እንዳይፈፀም መከላከልና አጥፊን መቅጣት ነው። ለእነርሱ ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ማስካስ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ የህጉ አላማ ነው።[5] በአንዳንድ ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ያለጥፋት አላፊነት እንዲኖር የሚደግፉት ሰዎች በበኩላቸው የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ተቀዳሚ አላማ ገለሰቦች ለሚደርስባቸው ጉዳት ዋስትና እንዲኖራቸው ማድረግ፣ ማለትም ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሣ ማስከፈል፣ ነው ይላሉ። በዚህኛው አመለካከት መሠረት አጥፊዎችን መቅጣት የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ዓላማ አይደለም። ይኸኛው የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ የሚያስተናግደው ጉዳይ ነው። የፍትሐብሄር አላፊነት የሚያስከትለው ውጤት ጉዳት የደረሰባቸውን ወገኖች ማስካስ ነው። በመሆኑም ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግን ጥፋት እንዳይፈፀም እንዲከላከል ሆኖ እንደተቀየሰ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ አድርጎ መመልከት ስሕተት ይሆናል።[6]

ይሁን እንጂ የውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ሕግ ተቀዳሚ ተግባር ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ካሣ ማስከፈል ነው ሲባል፣ ያለበቂ ምክንያት ሰዎች አላፊ እንዲሆኑ ይደረጋል ማለት እንዳልሆነ መገንዘብ ያሻል። "ቅጣት" የሚለው ቃል ካለው ስሜት አንፃር ጉዳዩ ከታየ ደግሞ፣ በተለይ አላፊነቱ በጥፋት ላይ የተመሠረተ በሚሆንበት ጊዜ፣ አጥፊው ለፈፀመው ጥፋት አይቀጣም ማለትም አይደለም። የገንዘብ መቀጮ አለ። ምንም እንኳን በወንጀል ህግ እንደሚታየው አጥፊው ነፃነቱን የሚያጣ ባይሆንም፣ በራሱ ጥፋት ጉዳት ላደረሰበት ሰው ካሣ እንዲከፍል ይደረጋል። ይህም የሀብቱን መጠን ይቀንስበታል። በዚህ ስሜቱ አጥፊው ተቀጥቷል ማለት ይቻላል።

ይህም ሁኔታ ግለሰቦች በሌሎች ወገኖች ላይ ጉዳት ለማድረስ እንዳይደፋፈሩ ያደርጋቸዋል። ይኸ ግን በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ የውል ላይኖር የሚደርስ አላፊነት ህግ ተግባር ነው።

ሦስተኛው ዓይነት አላፊነት፥ ማለትም ሌሎች ሰዎች ለፈፀሙት ተግባር አላፊ መሆን፥ በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ የሚያጋጥም ነው። ጠቅለል ባለ አነጋገር አንድ ሰው በሌሎች ሰዎች ለተፈፀሙ ተግባሮች በፍትሐብሄር አላፊ የሚሆንባቸው ሦስት ሁኔታዎች አሉ። አንደኛ፥ ወላጆች ወይም በወላጆች እግር የሚተኩ[7] ሌሎች ሰዎች አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች[8] ለሚያደርሱት ጉዳት አላፊ ይሆናሉ። ሁለተኛ፥ አንድ አሠሪ ሠራተኛው ለሚያደርሰው ጉዳት አላፊ ይሆናል።[9] ከነዚህም በተጨማሪ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ የሚሆንበት ሦስተኛ ሁኔታም አለ። ይኸም የአንድ ጽሁፍ ደራሲ ስም አጥፍቶ የሚገኝበት ጉዳይ ነው። እንዲህ ባለው ሁኔታ ደራሲው በጽሁፉ ውስጥ ለፈፀመው የስም ማጥፋት ተግባር የጋዜጣው መሪ፥ የተባራሪው ማስታወቂያ /ፓምፍሌት/ አታሚ፥ ወይም የመጽሐፉ አውጪ /ፓብሊሸር/ አላፊ ይሆናል።[10] የሁዋለኞቹ ሁለት ሁኔታዎች በዚህ ጽሁፍ ውስጥ አይወሱም። የምናተኩረው አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች በሚኖረው አላፊነት ላይ ብቻ ነው።

ለመሆኑ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት መሠረቱ ምንድን ነው? የትኞቹ ሰዎች ናቸው አላፊ የተደረጉት? ለምንስ አላፊነት ተጣለባቸው?

## የተለያዩ አመለካከቶች

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊነቱን ለመጣል ባጠቃላይ ሁለት አመለካከቶች አሉ። እነሱም /1/ ጥፋት ተፈፅሟል በሚል የሕግ ግምት፥ እና /2/ ጥፋት ለመፈፀሙ ማረጋገጫ ይቅረብ፥ በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። እነዚህንም ተፐለን በየተራ በአጭሩ እንተነትናቸዋለን።

1/ ጥፋት ተፈፅሟል በሚል የሕግ ግምት ላይ የተመሠረተ አላፊነት

በዚህ አመለካከት መሠረት እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት የተመሠረተው እካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ የሚቆጣጠሩት ሰዎች ጥፋት ፈፅመዋል በሚል የሕግ ግምት ላይ ነው። ይኸኛው አስተሳሰብ የሲቪል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች በአብዛኛው ሲሠራበት ይታያል። ሆኖም ጥቃቅን ልዩነቶች አሉ። የፈረንሳይና የጀርመን የፍትሐብሄር ሕጎች ተፅዕኖ ትልቅ በሚሆኑባቸው አገሮች የልጁ ወላጆችና ሌሎች አሳዳጊዎች የመጀመሪያ ደረጃ አላፊነት አለባቸው።[11] በአብዛኛዎቹም የምሥራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት አገሮችና በሶቪየት ኅብረት እነዚህ ሰዎች የመጀመሪያ ደረጃ አላፊነት የሚኖርባቸው ልጁ የተወሰነ ዕድሜ እስኪሞላው ድረስ ነው። የተለመደው የዕድሜ ገደብም 13 ወይም 15 ዓመት ነው። በነዚሁ አገሮች ህጎች መሠረት ልጁ ዕድሜው ከ13 ወይም ከ15 ዓመት በታች ከሆነ ሙሉውን አላፊነት አይኖርበትም።[12] ልጁ 13 ወይም 15 ዓመት ከሞላው በኋላ ግን ላደረሰው ጉዳት አላፊ ይሆናል። እንዲሁ ሲሆን የወላጆቹ አላፊነት በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ይሆናል። ይህም ማለት ወላጆቹ በአላፊነት የሚጠየቁት ልጁ ያደረሰውን ጉዳት ለመካስ የልጁ ሀብት የማይበቃ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው።[13] የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓቶችን በሚከተሉ ብዙ አገሮች ግን እካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለሚያደርሰው ጉዳት ከአላፊነት ነፃ እንዲሆን ካለመደረጉም በላይ ልጁ ያለው ሀብት ካሳውን ለመክፈል በቂ ቢሆንም ባይሆንም ወላጆቹ ከአላፊነት አያመልጡም።

ከእንደነዚሁ ዓይነቶቹ ጥቃቅን ልዩነቶች በስተቀር በሁለቱም ሁኔታዎች ወላጆቹ ጉዳት ያስከተለው የልጁ ድርጊት እንዳይፈፀም ሊያደርጉ የሚችሉበት ሁኔታ አለመኖሩን ካረጋገጡ ከአላፊነት ነፃ ይሆናሉ። ይህም ማለት ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት ተቃራኒ ማስረጃ የማይቀርብበት ነው ማለት አይደለም።[14]

## /2/ ጥፋት ለመፈፀሙ ማረጋገጫ ይቅረብ በሚል አስተሳሰብ ላይ የተመሠረተ አላፊነት

በኮመን ሎ እና በስካንዲኔቪያን አገሮች የወላጅና ተወላጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ወላጆች ልጃቸው ላደረሰው ጉዳት አላፊ አይደረጉም። አላፊ የሚሆኑት ጉዳቱ የደረሰው እነሱ በፈፀሙት ቸልተኝነት የተሞላበት የቁጥጥር ተግባር ምክንያት መሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። በወላጆቹ በኩል የተፈፀመው የመቆጣጠር ተግባር ቸልተኝነት የተሞላበት እንደነበረ የማረጋገጡ ሸክም የወደቀውም በራሱ በተጎጂው ላይ ነው። በዚህ ረገድ ተጎጂውን ለማገዝ የተደነገገ ምንም ዓይነት የሕግ ግምት የለም።[15]

### የኢትዮጵያ አመለካከት

በእኛ ሕግ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የመቆጣጠር ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች በአማራጭ አባት፣[16] እናት፣ ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጪ የሚኖር ከሆነ፣ ልጁን በአምነት የተቀበለው የልጁ ጠባቂ፣ የቀለም ትምህርት መምህሩና፣ የሙያ ሥራ አስተማሪ ናቸው።[17] አሠሪውም ከነዚህ ሰዎች ጋራ ተጠቃሏል። ዳሩ ግን ሠራተኛው አካለ መጠን ያላደረሰ ወይም ያደረሰ ቢሆንም ባይሆንም አሠሪው ለሠራኛው ተግባሮች አላፊ የሚሆንባቸው ሁኔታዎች አንድ ዓይነት[18] ስለሆኑ ይህን ጉዳይ በዚህ ጽሁፍ አናወሳውም።

አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለመጣበት አላፊነት ሌላ ሰው አላፊ እንዲሆን በመደረጉ ምክንያት ብቻ የኢትዮጵያ ሕግ አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ ከአላፊነት ነፃ ያላደረገው መሆኑ ከመጀመሪያው ሊታወቅ ይገባል። አላፊ ከሚሆነው ሰው ጋራ በመሆን ልጁ ራሱ ላደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ይገደዳል።[19]

አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት የመጣበት እንደሆነ አባቱ አላፊ እንደሚሆን በፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2124 ተደንግጓል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሁለት መንገዶች ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ይመጣበታል። ጥፋት ፈፅሞ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። እንዲህ ሲሆን፥ በራሱ ጥፋት አላፊነት ውስጥ ገባ ማለት ነው። እንዲሁም አንድ ለየት ያለ ሥራ ሊያከናውን ይችላል፥ ወይም የአንድ ንብረት ባለሀብት ወይም ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ታዲያ በዚህ በሚያከናውነው ለየት ያለ ሥራ ወይም በባለሀብትነት በያዘው ወይም በሚገለገልበት[20] ንብረት አማካይነት በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። በዚህ ጊዜ አላፊነት ውስጥ የሚገባው ጥፋት ስለፈፀመ ሳይሆን ጉዳቱ የደረሰው በሚያከናውነው ሥራ ወይም በባለሀብትነት በያዘው ወይም ለራሱ ጥቅም ሲል በሚገለገልበት ንብረት አማካይነት በመሆኑና በዚህ ዓይነቱ ሁኔታም ያለጥፋት አላፊነት እንደሚኖር ሕጉ ስለሚደነግግ ነው።[21]

ታዲያ ሕጉ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ሲመጣበት አባት አላፊ ይሆናል ብሎ ሲደነግግ ምን ማለቱ ነው? በጥፋት ላይ ለተመሠረቱት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ዓይነት የልጁ ውል ሳይኖር የሚደርሱ አላፊነቶች አላፊ የሆናል ማለት ነው? ወይስ በሌላ አነጋገር አላፊነቱ የመጣው ልጁ ጥፋት ፈፅሞ ቢሆንም ባይሆንም ልጁ አላፊነት በመጣበት ቁጥር አባቱ ያለጥፋቱ አላፊ ይሆናል ማለት ነው?

በኢትዮጵያ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት ሕግ ላይ ሼጋ መጽሐፍ እንደፃፉት እንደፕሮፌሰር ክሺቼናሺች አመለካከት ከሆነ፥ አካለመጠን ላላደረሰ ልጅ ያለው አላፊነት "በጥፋት ላይ የተመሠረቱትን ብቻ ሳይሆን ውል ሳይኖር የሚደርሱትን ማናቸውንም የልጁን አላፊነቶች ሁሉ ያጠቃልላል።"[22] ይህም ማለት፥ ለምሳሌ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ የአንድ ሞተር ተሽከርካሪ ባለሀብት ቢሆንና ይኸው የልጁ ሀብት የሆነው ሞተር ተሽከርካሪ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ቢያደርስ፥ የልጁ አባት አላፊ ይሆናል ማለት ነው። ምክንያቱም የእርሱ ንብረት የሆነው ሞተር ተሽከርካሪ በሌላ

ሰው ላይ ጉዳት ካደረሰ ልጁ የሞተር ተሽከርካሪው ባለሀብት በመሆኑ ያለጥፋቱ አላፊ ስለሚሆን ነው።[23] ሁኔታው ይኸ መሆኑን ለማብራራት ፕሮፌሰር ክሸቼኖቪች በግርጌ ማስታወሻ የሚከተለውን ምሳሌ ያቀርባሉ።" ልጁ የአንድ እንስሳ ባለሀብት ሊሆንና በቁጥር 2071 ሥር "ጥብቅ" አላፊነት ሊመጣበት ይችላል። ይህ ሁኔታ አባቱን /ቁጥር 2124/ ወይም ሌላ "አሳዳሪውን" /ቁጥር 2125/ አላፊ ለማድረግ በቂ ይሆናል።"[24] ፕሮፌሰር ክሺቼኖቪች እንዳደረጉት ሁሉ አንድ ሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2124ን ከቁጥር 2027/3/ ጋራ አጣምሮ በማንበብ እንዲህ ካለው መደምደሚያ ላይ ሊደርስ ይችላል። ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት የመጨረሻው ምንጭ የሆነው ቁጥር 2027/3/ አንድ ሰው አንድ ሌላ ሰው በጥፋት ምክንያት ወይም በሀግ በተደነገገው ሁኔታ አላፊነት ሲኖርበትና ሕጉ ለዚህ ሰው አላፊ እንዲሆን ሲያደርገው አላፊ ይሆናል "በማለት ይደነግጋል። እንግዲህ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አንድ ሰው ከቁጥር 2028 እስከ 2065 ወይም ከቁጥር 2066 እስከ 2089 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊነት ሲመጣበት፥ ማለትም በጥፋቱ ወይም ጥፋት በሌለበት ሥራው /ለምሳሌ ቁጥር 2066 እና 2067/ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ፥ ወይም እርሱ ጥፋት ሳይኖርበት የራሱ ሀብት የሆነ ንብረት /ቁ. 2071፥ 2077፥ 2081/፥ ወይም ለግል የሚገለገልበት የሌላ ሰው ንብረት /2072 እና 2082/፥ በሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ ሕጉ ለዚህ ሰው አላፊ ትሆናለህ ያለው ሌላው ሰው አላፊ ይሆናል ማለት ነው። የሆነ ሆኖ፥ ምንም እንኳን ይህ ድንጋጌ የሚናገረውን የሚል ቢመስልም፥ አንድ ሠራተኛ ወይም ደረሲ ከቁጥር 2066 እስከ 2089 ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት አላፊነት ሲመጣበት ሌላው ሰው አላፊ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ የለም። እንደእውነቱ ከሆነ ሠራተኞችን በሚመለከት አሠሪው አላፊ የሚሆነው ሠራተኛው የተሰጠውን ሥራ ሲያከናውን /ቁጥር 2129፥ 2130 እና 2131 ተጣምረው ሲነበቡ/ ወይም የተመደበበትን የመንግሥት ሥራ በሚያከናውንበት ጊዜ /ቁጥር 2126/2/ እና ቁጥር 2127/1/ ተጣምረው ሲነበቡ/ ጥፋት ፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው። ሠራተኛው ለሚፈጽማቸው ሌሎች ጥፋቶች አላፊነት አይኖርም። ደራሲያንን በሚመለከትም ለሌላ ሰው ተግባር አላፊ እንዲሆን የተደረገው ተከሳሽ አላፊ የሚሆነው ለስም ማጥፋት ብቻ ነው /ቁጥር 2135/። እንግዲህ "ልዩነት" ያለው አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን በሚመለከት ብቻ ይመስላል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በራሱ ጥፋት

ወይም ያለተፋቱ አላፊነት ውስጥ ሲገባ /ለምሳሌ ከ2066 እስከ 2089 ባሉት ቁጥሮች መሠረት/ በቁጥር 2124 መሠረት በፍትሐብሔር በኩል ላለው ጉዳይ አባቱ አላፊ የሚሆን ይመስላል። በተጨማሪም፣ አንድ ሰው ቁጥር 2124 እና 2027/3/ን አጣምሮ በማንበብ የሚደርስበት ትርጉም ይኸ ከሆነ ደግሞ፣ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አባት ብቻ ሳይሆን በልጁ ላይ አላፊነቱ በመጣ ጊዜ ልጁ በማን ቁጥጥር ሥር እንደነበር በማየት ብቻ በቁጥር 2125 ሥር የተዘረዘሩት ሌሎች የልጁ "አሳዳሪዎችም" ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባ ቁጥር የፍትሐብሔር አላፊነት ይኖርባቸዋል ማለት ነው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የልጁ ሌሎች "አሳዳሪዎች" በልጁ አባት ምትክ በአላፊነት ስለሚጠየቁ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሕጉ በሁለንተናዊ አቋሙ ሲተረጎም የልጁን አባትና የሌሎቹን አሳዳሪዎች አላፊነት አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አንድን ድርጊት በገቢር ፈጽሞ አላፊነት ውስጥ በሚገባባቸው ሁኔታዎች ላይ ብቻ የገደበው ይመስላል። ለሌላ ሰው ተግባር[25] አላፊ ስለመሆን የሚለው የክፍል 4 ርዕስ ሲጤንም ትርጉሙ ይኸው ይመስላል። ከዚሁ ጋራ የሚጣጣመው የቁጥር 2124 የአማርኛ ትጅም አባቱንና ሌሎች አሳዳሪዎቹን አላፊ ለማድረግ በልጁ በኩል በገቢር የተፈፀመ ድርጊት እንዲኖር ያዛል። "አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ ..." በማለትም ይደነግጋል /ሥርዝ የተጨመረ/። እንዲሁም በዚሁ ክፍል ሥር የሚገኘው ቁጥር 2136 የእነዚህን ሰዎች አላፊነት ልጁ ድርጊት ፈፅሞ ጉዳት በሚያደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ ገድቦታል።[26]

የሆነው ይሁንና ለመሆኑ ወላጆችና አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን የመቆጣጠር ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች ሰዎች አላፊ እንዲሆኑ የተደረገበት መሠረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? እስቲ በብዙ አገሮች የፍትሐብሔር ህጎች ላይ ተፅዕኖ ያሳደረውን የ1804 ቱን የፈረንሳይ የፍትሐብሔር ሕግ ካረቀቁት ሰዎች መካከል ትሬይልሃርድ የተባሉት ሰው በዚህ ጉዳይ ላይ ብለውት የነበረውን እንመልከት። እርሳቸው

እነዚያ የአላፊነት ሸክም የተጫለባቸው ቢያንስ፥ ገሚሶቹ በልልነት፥ ገሚሶቹ ደግሞ በእትል አመራረጥ፥ ሁሉም ደግሞ በደንታቢስነት ሊነወሩ ይችላሉ። መጥፎ አርአያ ባለመሆንና ጠንቀኛ የሆኑ አስተሳሰቦችን ባለማስተማር ራሳቸውን ከሕሊና ወቀሳ ነፃ ያደረጉ እነዚያ ብቻን ናቸው። ይህ አላፊነት የቤተሰብ አባወራዎችን ይበልጥ አስተዋይና ጥንቁቅ እንዲሆኑ ...፥ ደግሞም የግዴታቸውን አጥናፍና ቅድስና በይበልጥ እንዲገነዘቡ ያድርጋቸው! በጎ ሥነ ምግባርን እንዲቀስሙ በማድረግ መልካም ዜጎች እንዲሆኑ ካላዘጋጀናቸው በቀር ለልጆቻችን የምንቸረው ሕይወት በረከት አይደለም፥"[27] ብለው ነበር /ሰርዝ የተጨመረ/።

እንግዲህ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የመቆጣጠር ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ልጆች ለሚፈፀሙት ተግባር በፍትሐብሄር በኩል አላፊ እንዲሆኑ የተደረገው በእነዚህ ምክንያቶች[28] ነበር፥ አሁንም ነው። "እንዲህ ያሉት ሰዎች በልጆቻቸው አዕምሮ ውስጥ የሌሎች ሰዎችን ጥቅም የማክበር በጎ አስተሳሰብ እንዲሰርፅ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፤ በሌሎች ጥቅም ላይ ልጆች ጉዳት ካደረሱ ሁኔታው እነኚህ ሰዎች ተገቢ ሥነ ሥርዓት የማስተማር ግዴታቸውን አለመወጣታቸውን የሚያንፀባርቅ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ግዴታን አለመወጣት ደግሞ እንደጥፋት ይቆጠራል።"[29]

ከዚህ በላይ ከተገለፀው መሠረተ ሀሳብ ጋራ በመጣጣም ቀደም ሲል እንዳየነው በሲቪል የሕግ ሥርዓት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ባደረሰ ቁጥር የልጁ ወላጅ ወይም አሳዳሪ የመቆጣጠር ተግባሩን በማከናወን ረገድ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ይገመታል። ይሁን እንጂ የጉዳቱን መድረስ ለማስቀረት ፈፅሞ አይቻል እንደነበረ[30] በማስረዳት ጥፋት ፈፅመሃል የሚለውን የሕግ ግምት ለመቃወምና ከአላፊነት ነፃ ለመሆን ይችላል።

በሶሺየት ኅብረትና በምሥራቅ አውሮፓ የሶሻሊስት አገሮች አንድ ወላጅ እካለመጠን ያላደረሰ ልጁ ላደረሰው ጉዳት አላፊ የሚሆነው ልጁን በመቆጣጠር ረገድ ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ ነው።

በኮመን ሎ እና በስካንዲኔቪያን አገሮች ወላጁ የወላጅ ተወላጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ ልጁ ላደረሰው ጉዳት አላፊነት አይኖርበትም። እዚያ የወላጁ አላፊነት የተመሠረተው በራሱ የቸልተኝነት ተግባር፣ ማለትም ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ባለማድረጉ፣ ላይ ነው። ወላጁ በልጁ ላይ ያለውን የመቆጣጠር ተግባር ችላ ባይል ኖሮ ለልጁ የጥፋት ተግባር በአላፊነት ባልተጠየቀም ነበር።

ቀደም ሲል የተገለፀው የሚያረጋግጠው በሁሉም የሕግ ሥርዓቶች የወላጁ ወይም የአሳዳሪው አላፊነት ገደብየለሽ አለመሆኑን ነው። አላፊነቱ ጉዳት በመድረሱ ወይም የወላጅና ተወላጅ ወይም የአሳዳሪና የልጅ ግንኙነት በመኖሩ ምክንያት ብቻ የሚመጣ ሳይሆን፣ ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው አካለመጠን ያላደረሰውን ልጅ በመቆጣጠር ረገድ የፈፀመው ጥፋት መኖሩ ሲረጋገጥ /ወይም ጥፋት ተፈፅሟል የሚል ግምት ሲወሰድ/ ብቻ የሚፈጠር ነው።

ቀደም ሲል ከተገለፁት የሕግ ሥርዓቶች የእኛ ሕግ የተለየ ነውን? በተለይ የእኛ የፍትሐብሄር ሕግ የኮንቲኔንታል የሕግ ሥርዓት ተፅዕኖ ያለበት መሆኑ ከግምት ውስጥ ሲገባ፣ ይህን አላፊነት ጥፋት አለ በሚል የሕግ ግምት ላይ ከመሠረቱት የሕግ ሥርዓቶች ልዩ ነው ማለት ይቻላል? በዚህ ጉዳይ ላይ የእኛ ሕግ በመላው ዓለም ካሉት የሕግ ሥርዓቶች ሁሉ ጨርሶ የተለየ ነው በማለት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነት በመጣበት ቁጥር፣ አላፊነቱ የመጣው በጥፋትም ሆነ ያለጥፋት፣ የልጁ አባት ወይም አሳዳሪ አላፊ ይሆናል የሚል አቋም መያዝ ሁኔታውን ትርጉም የለሽ አያደርገውምን? አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት የመቆጣጠር ተግባሩ ቸልተኝነት የተሞላበት ነው በሚል የሕግ ግምት ላይ የተመሠረተ ነው እንደሚል አድርጎ የእኛን ሕግ መተርጎም አይቻልምን?

የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለውን አላፊነት የሚወስኑትን የእኛን የፍትሐብሄር ሕግ ድንጋጌዎች አላፊነቱ የተመሠረተው በሲቪል የሕግ ሥርዓቶች እንደተደረገው በቸልተኝነት የመቆጣጠር ሁኔታ ላይ እንጂ እካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ውስጥ የገባ መሆኑን በሚያሳይ ሐቅ ላይ ብቻ፣ ወይም የወላጅና ተወላጅ ወይም የሞግዚትና የልጅ ግንኙነት መኖሩ በመረጋገጡ ሐቅ ላይ ብቻ የተመሠረተ አይደለም ብሎ ለመተርጎም የሚያስችል መንገድ አለ ብሎ ያስባል። በርግጥም ሁኔታው ይህ ለመሆኑ እካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊ እንዲሆኑ የተደረጉት ሰዎች አመራረጥ ፍንጭ ይሰጣል። መጀመሪያ ነገር አላፊነቱ ምትክ ሲሆን እካለመጠን ባደረሰው ልጅ ላይ የአባትነት ሥልጣን ወይም የመቆጣጠር ኃላፊነት መኖርን ይጠይቃል። በመጀመሪያ ደረጃ አላፊ የተደረገው አባት ነው። ይህም አባት የቤተሰብ የበላይ አስተዳዳሪ[31] በመሆኑ ሮማውያን ፓትሪያ ፖተስታስ ከሚሉት የአስተዳዳሪነት ሥልጣን ጋራ ግንኙነት ያለው ይመስላል። በርዕሰ ቤተሰብነቱ አባት እካለመጠን ያላደረሱ ልጆቹን ምግባርና እንቅስቃሴዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን የሚሰቱንም ተግባሮች ጭምር የመቆጣጠር ሥልጣን አለው።[32] ይህን በተጨባጭ የሚታወቀውንና ሕጋዊም የሆነውን ሥልጣን በመገንዘብ ይመስላል በእኛ ኅብረተሰብ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ልጆች ለአባቶቻቸው የሚሰጡት አክብሮት ለእናቶቻቸው ከሚሰጡት ልቆ የሚታየው። ሕጉም አባትን እካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ለሚያደርሰው ጉዳት አላፊ እንዲሆን ያደረገው ይህንኑ አባታዊ ሥልጣን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይመስላል።

እናት ተጠያቂ የምትሆነው በአባት እግር ተተክታ[33] ሲሆን፣ ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባበት ጊዜ በልጁ ላይ አባታዊ ሥልጣን የነበራት ከሆነ ብቻ ነው። ብዙውን ጊዜ እናት አባታዊ ሥልጣን የሚኖራት አባት ከሞተ፣ ችሎታ ካጣ፣ ከጠፋ፣ ወይም ቤተሰቡን በትና በመሄዱ የተፈረደበት እንደሆነ ነው።[34] ባልና ሚስቱ አብረው በትዳር መኖራቸው በፍቺ ምክንያት አክትሞ የቤተዘመድ የሽምግልና ዳኞች የልጁ ሞግዚት እንድትሆን በሚወስኑበት ጊዜም እናት ይህ የአባታዊ ሥልጣን ይኖራታል።[35] በተጨማሪም፣ ከጋብቻው በፊት በወለደችው ልጅ ላይ ሙሉና ብቸኛ ሥልጣን

አሳት።[36] እንግዲህ በእነዚህ ሁኔታዎች ነው እናት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅዋ ለፈፀማቸው ተግባሮች አላፊ የምትሆነው።

ሌሎች የልጁ አሳዳሪዎችም በአባት አላፊነት ምትክ አላፊ እንዲሆኑ ተደርጓል። አላፊነታቸው ግን ልጁ አላፊነት ውስጥ በገባ ጊዜ በልጁ ላይ የመቆጣጠር ሥልጣን የነበራቸው ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጭ የሚኖር ከሆነ ማድረግ የሚገባውንና የማይገባውን መቆጣጠር ያለበት ልጁን እንዲጠብቅ በእምነት የተሰጠው ሰው ነው። በመሆኑም በተበቃው ሥር እንዳለ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ አላፊነት ውስጥ ከገባ አላፊ የሚሆነው ይኸው ሰው እንጂ የልጁ ወላጆች አይደሉም።[37] ልጁ በቁጥጥራቸው ሥር ስላልነበረ አላፊነት ውስጥ የገባው ተገቢ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ነው ለማለት አይቻልም።

አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በትምህርት ቤት ውስጥ እያለ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ ከሠራ አላፊ የሚሆነው የቀለም ትምህርት መምህሩ ነው።[38] አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች አብዛኛውን ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት የአደጋ ሁኔታዎች ከፍተኛ በሆኑበት በትምህርት ቤቶች ወይም በመሰል የትምህርት መስጫ ተቋሞች መሆኑ ግልፅ ነው። በመሆኑም የቀለም ትምህርት መምህሩ አላፊነት የሚያስነሳቸው ችግሮች ልዩ ትኩረት ሊሠጣቸው ይገባል። የዘመኑ የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት ቢያንስ አንድ መምህር መመደብን የሚጠይቅ በመሆኑ፥ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምሩት መምህራን ቁጥር ብዙ ነው። የቀለም መምህሩም የትምህርት ቤቱ አስተዳዳሪም አንድ ሰው ብቻ የነበረባቸው ዘመናት ነጉደዋል። ይህ ዓይነቱን የትምህርት አሰጣጥ ሥርዓት በሥራ ላይ ማዋል ይቻል የነበረው በገጠማት በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ነበር። ስለዚህ፥ አሁን ባለው ሁኔታ የመቆጣጠር ተግባሩን ያጓደለውን መምህር ነጥሎ ማውጣት ቀላል አለመሆኑን ማስተዋል እያዳግትም። የአንድ ትምህርት ቤት መምህራን በሙሉ በጋራ አላፊ ሊሆኑ ይገባል? ወይንስ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ወይም አስተዳዳሪ ብቻውን አላፊ ይደረግ? እንዴት አድርጎ ነው በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ ሊቆጣጠር የሚችለው?

ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች እርስ በርሳቸው እየተናቆሩ አንዱ በሌላው ላይ ጉዳት የሚያደርሰው አስተማሪው በክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜ ሳይሆን በእረፍት ጊዜያቸው ወይም የክፍል ትምህርት ከመጀመሩ በፊት በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲያምቧቹ ነው። በነዚህ ሰዓታት መምህራኑ በተማሪዎቻቸው የመምቧቻ ሥፍራ እንዲገኙና ተግባሮቻቸውን እንዲቆጣጠሩ ይጠበቅባቸዋል? በዚህ ምድብ ውስጥ የሚገኙት የግልና የመንግሥት ሠራተኞች አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን የሚያስተምሩ በመሆኑ ብቻ የእንዲህ ያለው አላፊነት ቀንበር ተሸካሚ እንዲሆኑ ማድረግ አግባብ ነውን? ካሣ የመክፈሉን አላፊነት ወደ መምህሩ ቀጣሪ ማዛወር ተገቢ አይሆንም?

በጀርመን አገር መምህራን እንደመንግሥት ሠራተኞች ይቆጠራሉ። በመምህሩ የሚከናወነው የመቆጣጠር ጥፋትም የመንግሥት የሥራ ግዴታዎችን እንደመጣስ የሚታይ ነው። በዚህም መሠረት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ እያሉ ባደረሱት ጉዳት ምክንያት የሚመጣውን የመምህራን አላፊነት መንግሥት የሚሸከመው ይሆናል።[39] በተጨማሪም በመምህራን በኩል ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት በጀርመን አገር ተፈፃሚነት እንዳይኖረው ተደርጓል። ፈረንሳይም እንዲሁ መምህራንን በሚመለከት ጥፋት አለ የሚለው የሕግ ግምት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው አድርጋለች። በዚህም ምክንያት አንድ ተማሪ በፈፀመው ተግባር ጉዳት የደረሰበት ሰው በመቆጣጠር ረገድ መምህሩ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያስረዳ ማረጋገጫ በቅድሚያ ማቅረብ አለበት።[40]

እኛስ ይህን አስተሳሰብ በመከተል፣ ባይሆን እንኳን ለወደፊቱ፣ በመምህሩ ፋንታ ትምህርት ቤቱን አላፊ ማድረግ ይኖርብን ይሆን? ትምህርት ቤቱ አላፊ የሚሆን ከሆነ መምህራን ያለባቸውን የመቆጣጠር ተግባር በሚገባ ላያከናውኑ ይችላሉ የሚል ስጋት ይፈጠር ይሆን? ይኸ የእውን ፍራቻ ከሆነ የመምህሩ አላፊነት እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል። ይህ የሚሆነው ግን የመምህሩ ጥፋት የተለየ ከብደት ያለው ሆኖ በሚገኝበትና መምህሩ በመቆጣጠር ተግባሩ ላሳየው ጉድለት በቅድሚያ ማረጋገጫ በማቅረብ የማስረዳቱ ሸክም የተበዳዩ ወይም የትምህርት ቤቱ እንዲሆን በተደረገበት ሁኔታ ብቻ

መሆን ይኖርበታል። አሁን በሚሠራበት ሕጋችን ግን አንድ መምህር ተማሪዎቹ ላደረሱት ጉዳት አላፊ መሆን ብቻ ሳይሆን ተገቢ ያልሆነ የመቆጣጠር ተግባር ተፈፅሟል የሚለውን የጥፋት መኖር ግምት እንኳን ለመቃወም የሚችልበት መንገድ የለውም።

አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ የሙያ ትምህርት በለማጅነት በሚቀሰምበት ጊዜ ጉዳት ቢያደርስ የሙያ አስተማሪውም ልክ እንደ ቀለም መምህሩ አላፊነት ይኖርበታል። ይሁን እንጂ፣ በለማጅነት የሚቀጠሩት ዕድሜአቸው ከአሥራ አራት ዓመት በላይ የሆኑት በመሆኑ የሙያ አስተማሪው ያለበት አላፊነት የቀለም መምህሩ ያለበትን አላፊነት ያህል የሠፋ አይመስለኝም። እነኚህዎቹ ልጆች አካለመጠን ለማድረስ እየተቃረቡና በአዕምሮ በሰል እያሉ በመሆኑ አላፊነትን ለመሸከምና ከአስነዋሪ ተግባር ራሳቸውን ለማቀብ ዝግጁ የሆኑ ይመስላል።

የአንቀጽ 13 ምዕራፍ 1 ክፍል 4፣ ርዕስ፣ ቁጥር 2136 እና የቁጥር 2124 የአማርኛ ቅጅ የአባት ወይም የሌላ የማንኛውም አሳዳሪ አላፊነት አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በሚፈፅማቸው ተግባሮች ጉዳት በሚያደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑን ይጠቁማሉ። አንድ ሰው እነዚህን ሁሉ በአንድነት ቢያጤን በሌሎች የሲቪል የሕግ ሥርዓቶች እንደሚታየው ሁሉ በኛም ሕግ አካለመጠን ላላደረሱ ልጆች ተግባሮች ያለው አላፊነት የመቆጣጠሩ ተግባር ቸልተኝነት /ማለትም የአጥፊነት ሁኔታ/ አለበት በሚል ግምት ላይ የተመሠረተና አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በራሱ ጥፋት አላፊነት ውስጥ በሚገባበት ሁኔታዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ እንደሚደርስ ግልፅ ነው። ያለው ልዩነት በእኛ ሕግ ከአቅም በላይ[42] በሆነ ምክንያት ካልሆነ በቀር ይህን የሕግ ግምት መቃወም የማይቻል መሆኑ ብቻ ነው።

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆችን እንዲቆጣጠር አላፊነት በተጣለበት ሰው ላይ የተጣለው ይህ አላፊነት ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ካሣ እንዲያገኙ ዋስትና መሆኑ ግልፅ ነው። ዳሩ ግን፣ እንዲህ ዓይነቶቹ ዋስትናዎች አዕምሮ ሊቀበላቸው በሚችለው

ገደቦች ውስጥ እንዲወሰኑ ርትዕና ፍትሕ ያስገድዳሉ። አካለመጠን ላላደረሱ ልጆች የሚኖረው አላፊነት በጥፋት ላይ የተመሠረተውን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ውል ሳይኖር የሚደርሱ አላፊነቶች ይሸፍናል የሚል አቋም ከተወሰደ፥ ለምሳሌ ሀብትነቱ የአንድ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ የሆነ እንስሳ ወይም ሞተር ተሽከርካሪ[43] በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ሲያደርስ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ ስለሚሆን፥ ልጁ ይህ አላፊነት በመጣበት ጊዜ በማን ተቆጣጣሪነት ሥር እንደነበረ በመመልከት ብቻ እንደነገሩ ሁኔታ ከልጁ ወላጆች አንዱ ወይም በቁጥር 2125 ሥር ከተጠቀሱት ሰዎች መካከል አንደኛው አላፊ እንዲሆን ይደረጋልማለት ነው። ፕሮፌሰር ክሽቼኖቪች በግርጌ ማስታወሻ ያሉትም ይኸንኑ ነው።[44] ይህ ዓይነት አላፊነት አግባብ መሆኑን ለማሳየት ምን አሳማኝ ምክንያት ሊቀርብ ይችላል? እንዲያው ዝም ብሎ ልጁ በትምህርት ገበታ ላይ በነበረበት ጊዜ እንዲህ ዓይነት አላፊነት የመጣበት መሆኑን መሠረት በማድረግ ብቻ የቀለም ትምህርት መምህሩ አላፊ መሆን ይኖርበታል? አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለማጅ ሆኖ በሚያገለግልበት የሥራ ቦታ ሳለ እንዲህ ዓይነቱ አላፊነት የመጣበት በመሆኑ ብቻ የሙያ አስተማሪው አላፊ ሊሆን ይገባል? ወላጆቹስ ቢሆኑ የእነዚህ ነገሮች ሀብትነት የልጃቸው በመሆኑ ምክንያት ብቻ አላፊ መሆን አለባቸው? የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች እነዚህን ሰዎች አላፊ ለማድረግ አሳማኝና አግባብ የሆነ አንዳች ምክንያት አይታየውም። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን በተደረገባቸው ሁኔታዎች እነዚህን ሰዎች አላፊ ማድረግ በእነሱ ላይ ማሕበራዊ ኢፍትሕ መፈፀም ይሆናል። በእርግጥም "እንዲህ ዓይነቱ የፍትሐብሄር አላፊነት በወንጀል ጉዳይ በአንድ ንፁሕ ሰው ላይ ከሚሰጥ የቅጣት ፍርድ ጋራ የሚተካከል ይሆናል።"

እንዲህ ባሉት ሁኔታዎች አላፊ መሆን ያለበት የንብረቱ ባለሀብት ወይም ጠባቂ ብቻ ነው። በአንዳንድ የተግባር ክንዋኔዎች ወይም በንብረቶች በመገልገል ምክንያት ጉዳት የሚደርሰው፥ የፕሮፌሰር ክሽቼኖቪችን አነጋገር ለመጠቀም "እጅግ ጠንካራ በሆነ የጥንቃቄ መመዘኛ እንኳን ተከሳሹን ጥፋተኛ ለማድረግ በማይቻልበት፥ ወይም እጅግ ደካማ በሆነ የማረጋገጫ መመዘኛ እንኳን የጥፋት ማስረጃ ለማግኘት በሚሳንበት ሁኔታ"[45] እንደሆነ ልብ ማድረግ ያሻል። ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቶች

ሁኔታዎች በተጠቀሱት ንብረቶች በመገልገል ወይም አንዳንድ ሥራዎችን በማከናወን ጥቅም የሚያገኘው ተከሳሹ ስለሆነ ተበዳዩ ተጎድቶ የሚቀርበት ምንም ምክንያት የለም። በእነዚህ ሁኔታዎች ኪሳራው ወደ ንብረቶቹ ባለሀብት ወይም ተገልጋይ ወይም ወደ ሥራው ተጠቃሚ እንዲዛወር ርትዕ ያስገድዳል።

ስለዚህ ከቁጥር 2124 እስከ 2125 ያሉትን እና በተጣማሪነት የቁጥር 2027/3/ ድንጋጌዎችን በጥንቃቄና በአንክሮ በማጤን /የክፍሉን ርዕስና ቁጥር 2136ን በመጨመር/ የተገናዘበ ፍቺ ካልሰጠናቸው በቀር ድንጋጌዎቹ የልጁ ወላጆችና ሌሎች አሳዳሪዎች አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ለሚመጣበት ውል ሳይኖር የሚደርስ አላፊነቶች ሁሉ አላፊዎች ናቸው የሚሉ መስለው ይታያሉ። በተለይ የእንግሊዝኛው ቅጂ ሲመረመር ይህንን መስዕከት መያዙ ግልፅ ነው። ወሳኝነት ያለው የአማርኛ ቅጂ ግን አላፊነቱን አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በሚፈፀማቸው ተግባሮች ጉዳት በሚደርስበት ሁኔታ ላይ ብቻ የገደበው ይመስላል። በአማርኛው ቅጂ መሠረት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ድርጊት ፈፅሞ አላፊነት ውስጥ ሲገባ የተፈፀመው ድርጊት ጥፋት ቢሆንም ባይሆንም አባቱ ወይም የልጁ አሳዳሪ አላፊ ይሆናል። ነገር ግን ልጁ ድርጊት ሳይፈፅም አላፊነት ቢመጣበት፣ ለምሳሌ የእርሱ እንስሳ ወይም ታክሲ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት አድርሶ እንደሚገኝበት ባለ ሁኔታ፣ ባለሀብት ከሆነው ከራሱ ከልጁ በቀር ማንም በአላፊነት አይጠየቅም።

በሌላ በኩል፣ የአንቀጽ 13 ምዕራፍ 1 ክፍል 4 ርዕስንና የቁጥር 2136ን ድንጋጌ ወደጎን በመተው የቁጥር 2124ን የእንግሊዝኛ ቅጂ ብቻ መመልከት እነዚህ ሰዎች ለሁሉም የልጁ አላፊነቶች ተጠያቂ ናቸው ከሚል መደምደሚያ ላይ ያደርሳል። ይህ መደምደሚያ በተግባር ላይ ይዋል ቢባል ደግሞ ሁኔታው ፍቺ አልባና ስሜት የለሽ ይሆናል።

## ማጠቃለያ

ከፍ ብሎ ከተሰጠው ትንታኔ በመነሳት እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል።

1. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2124 እና 2125 የተጠቀሱት ሰዎች ያለባቸው አላፊነት የመቆጣጠሩ ተግባር ተገቢ አልነበረም በሚል የተፋት ግምት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ በቁጥር 2125 ሥር የተዘረዘሩት ሰዎች በተለይም የቀለም መምህሩ፥ የሞያ አስተማሪውና ልጁን በእምነት የወሰደው የልጁ ጠባቂ አላፊ እንዲሆኑ ባልተደረገ ነበር። እንዲሁም የልጁ እናት አላፊ የምትሆነው በአባትየው ምትክ ባልሆነ ነበር። ይልቁንም አላፊነቷ የጋራ በሆነ ነበር። ከዚህም በተጨማሪ ዕብዶች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች አላፊነት በኖረ ነበር። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የሚያረጋግጡት የአባትና የሌሎች አሳዳሪዎች አላፊነት የተመሠረተው እነዚህ ሰዎች ያለባቸውን የመቆጣጠር ተግባር በአግባቡ ባይፈፅሙ በመቅረታቸው እንጂ የወላጅና ተወላጅ ወይም የአሳዳሪና የልጅ ግንኙነት በመኖሩ ወይም በተበዳዩ ላይ ጉዳት በመድረሱ ምክንያት ብቻ አለመሆኑን ነው።

2. አላፊነቱ የተመሠረተው የመቆጣጠሩ ተግባር ተገቢ አልነበረም በሚል የተፋት ግምት ላይ በመሆኑም አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን በተደረገባቸው ሁኔታዎች ወላጆች ወይም ሌሎች አሳዳሪዎች አላፊነት አይኖርባቸውም።

3. በእኛ ሕግ አካለመጠን ላላደረሰው ልጅ አላፊ እንዲሆን የተደረገው ተከሳሽ ጥፋት አለ የሚለውን የሕግ ግምት ለማፍረስ ተቃራኒ ማስረጃ ለማቅረብ አይችልም።

## <u>የማጠቃለያ ሀሳብ</u>

አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች ለሚፈፅሟቸው ተግባሮች ያለው አላፊነት ቁጥጥሩ ጉድለት አለው በሚል የተፋት ግምት ላይ የተመሠረተ ነው። የሲቪል የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች ሁሉ ሁኔታው ይኸንኑ ይመስላል። ይህን የተፋት ግምት ተፈፃሚ ማድረግ ተገቢ ነው። ምክንያቱም "ብዙውን ጊዜ ተበዳዩ ጉዳቱ ከመድረሱ

አስቀድሞ ከልጁ ወይም ከወላጆቹ ጋር ትውውቅ የሌለው ሊሆን ስለሚችልና የቁጥጥር ግዴታ መኖደሉን ለማስረዳት በማይችልበት ሁኔታ ላይ ስለሚገኝ በቁጥጥር ረገድ ስለተፈፀመው ጥፋት ማረጋገጫ ለማቅረብ ያስቸግረዋል። በዚህም ምክንያት ተበዳዩ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ከልጁ አሳዳሪዎች አኳያ ሲታይ ለእሱ ሸክሙ የበለጠ ይከብደብታል።[46] ይሁን እንጂ ግምቱን ለማፍረስ እንደማይቻል አድርጎ መደንገጉ ትክክል አይመስልም። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅን የመቆጣጠር ግዴታ የተጣለባቸው ሰዎች በእነርሱ በኩል የቁጥጥር ጉድለት አለመኖሩን የሚያሳይ ማረጋገጫ በማቅረብ ካለባቸው ኃላፊነት ነፃ እንዲሆኑ መፍቀድም አግባብና በሕሊና ዳኝነት የሚደገፍ ነው።

በወደፊቱ ኢትዮጵያ የተጋቢዎች እኩልነት በሕግ እንደሚረጋገጥ ተስፋ እናደርጋለን። በዚያን ጊዜም የወላጅነት ሥልጣን በአባትና በእናት በጋራ የሚሠራበት ይሆናል። እንዲህ ሲሆን አባትና እናት የሚኖርባቸው ኃላፊነት ምትካዊ በመሆን ፋንታ የጋራ መሆን ይኖርበታል።

መምህራንን በሚመለከት ግን ግምቱ አግባብ ያለው አይመስልም። በተለይ የግል ትምህርት ቤቶች ከሚያስተምሩት በቀር መምህራን የመንግሥት ተቀጣሪ ሠራተኞች ናቸው። ከሌሎቹ የመንግሥት ሠራተኞች ተነጥለው እንዲህ ያለው ከባድ የሆነ ኃላፊነት ለምን ይጫንባቸዋል? ቢያንስ ያለባቸውን ሸክም ለማቃለል መምህሩ በተማሪው ላይ ተገቢውን ቁጥጥር አለማድረጉን የማስረዳቱን ግዴታ በተበዳዩ ላይ ማድረግ ይገባል። ከዚህም ይልቅ ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ሲባል ካሣ የመክፈል ግዴታውን የመምህሩ ጥፋት እጅግ ከባድ በሆነበት ልዩ ሁኔታ ካልሆነ በቀር በትምህርት ቤቱ ላይ መጣሉ /የግልም ቢሆን የመንግሥት/ የተሻለ ይሆናል።

እላይ የተሰጡትን ምክንያቶች መሠረት በማድረግ የፍትሐብሔር ሕጉን አራተኛ መጽሐፍ እንዲያሻሽል የተሰየመው የሕግ አሻሻይ ኮሚቴ በቁጥር 2124 እና 2125 ምትክ የሚከተሉትን ድንጋጌዎች እንዲቀበላቸው እናሳስባለን።

## ቁጥር 2124 - የወላጆች አላፊነት

1) አባትና እናት አካለ መጠን ባላደረሰው ልጃቸው ላይ የጋራ የወላጅነት ሥልጣን ካላቸው ልጁ በጥፋቱ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት በሚያደርስበት ጊዜ፥ ጉዳቱ የደረሰው ተገቢ የሆነ ቁጥጥር ባለማድረጋቸው ምክንያት አለመሆኑን ካላስረዱ በቀር፥ በፍትሐብሄር በኩል በጋራ አላፊ ይሆናሉ።

2) በልጁ ላይ የወላጅነት ሥልጣን ያለው ከወላጆቹ አንደኛው ብቻ ከሆነ ይኸው ወላጅ ብቻውን አላፊ ይሆናል።

## ቁጥር 2125 - የልጁ ሌሎች አላፊዎች

1) የሚከተሉት ሰዎች በወላጆች ምትክ አላፊ ይሆናሉ።
   (ሀ) አካለ መጠን ያላደረሰው ልጅ ከቤተሰቡ መኖሪያ ቤት ውጭ ሲኖር በእምነት የተሰጠው የልጁ ጠባቂ፥
   (ለ) ልጁ በትምህርት ቤት ባለበት ጊዜ ትምህርት ቤቱ፥
   (ሐ) ልጁ የሙያ ሥራ በሚለማመድበት ጊዜ የሞያ አስተማሪው።

2. በዚሁ ቁጥር ንዑስ ቁጥር 1/ለ/ በተገለፀው ሁኔታ ጉዳት ለደረሰበት ሰው ካሣ የከፈለ ትምህርት ቤት የመምህሩ ጥፋት በጣም ከባድ መሆኑን ካረጋገጠ የከፈለውን የካሣ ገንዘብ መምህሩ እንዲተካለት ለመጠየቅ ይችላል።

በዚህም መሠረት በቁጥር 2027 /3/ ውስጥ "ወይም በሕግ መሠረት" የሚለው ሐረግ ምንም ዓይነት አግባብነት ስለሌለው መሠረዝ ይኖርበታል።

# ማስታወሻዎች

1. በእኛ ሕግ ጥፋት "ሕሊናን ወይም የተለመደውን፣ መልካም አሠራር ተቃዋሚ በሆነ ዓይነት ድርጊት መፈፀም ወይም አለመፈፀም" ተብሎ የተተረጎመ ሲሆን ይኸውም አውቆ ወይም በቸልተኝነት ድርጊት መፈፀምን ወይም አለመፈፀምን ያጠቃልላል። ቁጥር 2030/1/ን ከቁጥር 2029 ጋራ በማጣመር ይመለከቷል። በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት ጥፋት የሚመዘነው አጥፊ የተባለውን ሰው ዕድሜና የአእምሮ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ባለማስገባትና አንድ አስተዋይ ሰው ሊፈፅመው የሚገባውን መሠረት በማድረግ ነው። ቁጥር 2030 /2-3/ን ይመለከቷል። በመሆኑም ሕፃን ወይም ዕብድ የሆነ ሰው ጥፋተኛ ነው ተብሎ አላፊ ሊሆን ይችላል። በነገራችን ላይ ተለይቶ ካልተመለከተ በስተቀር ሁሉም ቁጥሮች የ1952ቱን የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ የሚመለከቱ ናቸው።

2. አንድን ሰው ያለጥፋቱ አላፊ የሚያደርጉት "ሥራዎች" /ሀ/ "አደገኛ" ናቸው የሚባሉት /ቁጥር 2069/፣ /ለ/ በእርግጥ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማስቀረት ሲባል ሆን ብሎ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ማድረስ /ቁጥር 2066/፣ እና በራስ ድርጊት በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ማድረስ /ቁጥር 2067/ ናቸው።

   አንድ ሰው ጥፋተኛ ሳይሆን በሚፈፅመው ድርጊት በሌላ ሰው አካል ላይ እንዴት ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ለአንባቢ እንግዳ ነገር ሆኖ ይታይ ይሆናል። ለምሳሌ ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ሕንፃ ግዶ በሚገኘው ሜዳ አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች እግር ኳስ የሚጫወቱበትን ሁኔታ እንውሰድ፣ እንደኛው ተጫዋች አክርሮ የመታት ኳስ ከሜዳው ክልል ወጥታ እየፈጠነ ይሽከረከር የነበረን መኪና የፊት መስተዋት ስለሰበረች በመስተዋቱ ስብርባሪ ሾፌሩ የአካል ጉዳት ደረሰበት እንበል። በዚህ ጉዳይ ጉዳቱ የደረሰው ፍፁም በሆነ አጋጣሚ ነው። በሁለቱም ወገኖች ዘንድ ጥፋት ያልተፈፀመ ሲሆን ለጉዳቱ መድረስ ምክንያት የሆነው ኳሷን የመለጋቱ ድርጊት ነው። የሆነ ሆኖ፣ አካለመጠን ያላደረሰው ልጅ በመኪናው ላይ ለደረሰው ጉዳት አላፊነት የሌለበት መሆኑን መገንዘብ ያሻል።

ሌላ ምሳሌ እንውሰድ፣ አንድ አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ ብስክሌት እየነዳ ሳለ የብስክሌቷ የፊት ጎማ በድንገት በመፈንዳቱ ሚዛኑን መጠበቅ ተስኖት በአንድ እግረኛ ላይ ወድቆ ጉዳት አደረሰ እንበል። እዚህም ቢሆን በሁለቱ ወገኖች የተፈፀመ ጥፋት የለም። ይሁንና በእግረኛው ላይ ለደረሰው ጉዳት ምክንያት የሆነው አካለ መጠን ያላደረሰው ልጅ የፈፀመው የብስክሌት መንዳት ድርጊትና የብስክሌቱ ጎማ በድንገት መፈንዳት መሆኑ ግልፅ ነው። በነገራችን ላይ አንድ ተበዳይ በተከሳሹ ድርጊት ምክንያት የአካል ጉዳት ሲደርስበት ካሣ ለመጠየቅ ተከሳሹ ጥፋት የፈፀመ መሆኑን ማስረዳት እንደማያስፈልገው ልብ ማድረግ ይገባል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት ሰው ራሱ ጥፋተኛ ሆኖ ካልተገኘ በቀር ተከሳሹ ጥፋት ኖረበትም አልኖረበትም አላፊ ይሆናል።

3. ላደረሱት ጉዳት አንድ ሰው ያለጥፋቱ አላፊ እንዲሆን የሚያደርጉት ንብረቶች እንስሳት /ቁጥር 2071/፣ ሕንፃዎች /ቁጥር 2077/፣ መኪናዎችና ሞተር ተሽከርካሪዎች /ቁጥር 2081/፣ እና በሰው የተሠሩ ዕቃዎች /ቁጥር 2085/ ናቸው።

4. ኤም ፐላኒዮል፣ እነ ኤፍ ኤች ላውሰን በአሞፅና ዋልተን ኢንተርዳክሽን ቱ ፍሬንች ሎ ሁለተኛ እትም ውስጥ እንደጠቀሱት /ኦክስፎርድ፣ ክላሬንደን ፕሬስ፣ 1963/ ገጽ 203።

5. ለምሳሌ አር.ኤፍ.ቪ. ሂውስተን ሳልመንድ.ኦን.ዘ.ሎ.ኦፍ ቶርትስ፣ 16ኛ እትም /ለንደን፣ ስዊት ኤንድ ማክስዌል፣ 1973/ ከገጽ 20-21 ይመለከቷል።

6. ለምሳሌ ጆርጅ ክሽቺኖቪች፣ ዘ.ኢትዮጵያን ሎ.ኦፍ.ኤክስትራ ኮንትራክቹዋል ሊያቢሊቲ /አዲስ አበባ፣ ሕግ ፋኩልቲ፣ 1970/ ገጽ 38 እና 61ን ይመለከቷል።

7. ብዙውን ጊዜ እነዚህ ሰዎች የቀለም ትምህርት መምህራን፣ የሙያ አስተማሪዎች፣ አስተዳዳሪዎችና፣ ልጁ ከቤተሰቡ ውጭ የሚኖር ከሆነ ልጁ በአደራ የተሰጠው ጠባቂ ናቸው።

8. አካለ መጠን ያላደረሰ ልጅ የሚባለው ዕድሜው 18 ዓመት ያልሞላው ሰው ነው። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 198ን ይመለከቷል። ሆኖ ግን፣ ከሞግዚት አስተዳደር ሥልጣን ነፃ ለወጣ ልጅ ምንም እንኳን ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላ ቢሆንም በሚፈፅመው ሥራ ለሚመጣበት ኃላፊነት ተጠያቂነት የሌለ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ይህ የሆነበት ምክንያትም ከሞግዚት አስተዳደር ሥልጣን ነፃ የወጣ ልጅ ሰውነቱንና የገንዘብ ጥቅሞቹን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ሁሉ ለማስተዳደር በሕግ አካለ መጠን እንዳደረሰ ሰው ሆኖ ስለሚቆጠር ነው። የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 329፣ 330፣ እና 333ን ይመለከቷል።

9. ከቁጥር 2126 እስከ 2127 እና 2129 እስከ 2131 ይመለከቷል። አንድ አሠሪ ጥፋት የሌለበት መሆኑን በማረጋገጥ ከኃላፊነት ነፃ ስለማይሆን በዚህ ረገድ ያለበት ኃላፊነት ፍፁም "ጥብቅ" ነው። አሠሪውን አጥፊ ሳይሆን ኃላፊ እንዲሆን ለማድረግ በቂ ምክንያቶች አሉ። አንደኛ፣ ጉዳት ያስከተለው የጥፋት ድርጊት የተፈፀመው ሠራተኛው ለአሠሪው ጥቅም ሥራ በማከናወን ላይ እያለ ነው። ሁለተኛ፣ የሠራው ሥራ ጉዳት ባያስከትል ኖሮ ብቸኛ ተጠቃሚ የሚሆነው አሠሪው ነበር። በመሆኑም ሠራተኛው የተመደበለትን ሥራ በማከናወን ላይ እያለ በተፈፀመ ጥፋት ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈለውን ካሣ በአሠሪው ጫንቃ ላይ መጣሉ አግባብ ሊሆን ይችላል።

10. ቁጥር 2135ን ይመለከቷል። ደራሲ በፈፀመው የስም ማጥፋት ምክንያት በመጽሐፍ አውጭው ላይ ኃላፊነት የተጣለው መጽሐፍ አውጭው መጽሐፉን በማተምና ለሕዝብ በማሠራጨት በተዘዋዋሪ መንገድ በስም ማጥፋቱ ተግባር ተካፋይ ስለሆነ ይመስላል። ከዚህም በላይ ስም አጥፊ የሆኑ ዐረፍተነገሮች የያዘውን መጽሐፍ በማተም የገንዘብ ጥቅም አግኝቷል።

የጋዜጣ መሪን በሚመለከት የተጣለበት አላፊነት ከቸልተኝነት ተግባር አኳያ ሲታይ አግባብ ይሆናል። ምክንያቱም ቸልተኛ ባይሆን ኖሮ ስም አጥፊ የሆነው ጽሁፍ በጋዜጣው ላይ እንዲወጣ ባልፈቀደም ነበር። ከዚህም በላይ በሁለቱም ሁኔታዎች ደራሲው ማንነቱን የማይገልፁባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ስለዚህ፣ የስም ማጥፋት በደል የተፈፀመበት ሰው እንደዚህ ካሉት ሰዎች ካሣ እንዲጠይቅ ይኸን ዓይነቱን እገዛ ማድረግ ያስፈልጋል።

11. ዣንፒየር ለጎል፣ "ሊያብሊቴ ፎር ፐርሰንስ እንደር ሱፐርቪዠን" ኢንተርናሽናል ኢንሳይክሎፒዲያ ኦቭ ኮምፓራቲቭ ሎ፣ ቮልዩም 11፣ እንድሬ ቱንክ እንዳዘጋጀው/ ዘ. ሄግ፣ ቦስተን፣ ለንደን፣ ጄ.ሲ. ቢ. ሞህር፣ እና ማርቲነስ ኒጆፍ፣ ቱቢንገን ፓቢሊሸርስ፣ 1973/ገጽ 7 ይመለከቷል።

12. ይህ ሁኔታ ከተወሰነ የዕድሜ ክልል በታች ያለ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ከአላፊነት ነፃ የተደረገ መሆኑን ይጠቁማል። ለምሳሌ በፖላንድ ዕድሜው ከ13 ዓመት በታች የሆነ፣ በሶቪየት ኅብረት ደግሞ ከ15 ዓመት በታች የሆነ ዕድሜ ያለው ልጅ አላፊነት የለበትም። የፖላንድን የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 426ን እና የሶቪየት ሕብረትን የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 450ን ይመለከቷል።

13. ለጎል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን ገጽ 7 ላይ ይመለከቷል።

14. ይህንን መጽሐፍ ከገጽ 8-25 ይመለከቷል። ከዚህ የሚለዩት ሉዊዚያናና ማላጋሲ ብቻ ናቸው /የሉዊዝያና ሲቪል ኮድ አንቀጽ 2318ን እና የማላጋሲን ጄኔራል ሩልስ ኦቭ ኦብሊጌሽን አንቀጽ 223ን ይመለከቷል።/ በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አስተሳሰብ ይኸ ልዩነት ኢትዮጵያንም ይጨምራል።/ ቁጥር 2124ን እና 2125ን ይመለከቷል/።

15. እላይ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 7 እና ከገጽ 25-29 ይመለከቷል።

16. ቁጥር 2124፣ የዚህ ቁጥር ሙሉ ድንጋጌ እንደሚከተለው ይነበባል፣ "አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ አላፊነትን የሚያስከትል ሥራ የሠራ እንደሆነ በፍትሐብሄር በኩል ለተሠራው ሥራ አላፊ የሚሆን አባት ነው።"

17. ቁጥር 2125፣ የዚህ ቁጥር ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል፣ "የሚከተሉት ሰዎች በአባት አላፊነት ምትክ ተጠያቂ ይሆናል፣

/ሀ/ በልጅዋ ላይ በአባትነት ሥልጣን በምትሠራበት ጊዜ፣ እናት፣

/ለ/ ልጁ ከቤተሰቡ ቤት ውጭ የሚኖር ከሆነ ልጁ በአደራ የተሰጠው ጠባቂ፣

/ሐ/ ልጁ ት/ቤት ሳለ ወይምየሞያ ሥራ በሚማርበት ጊዜ የቀለም ወይም የሞያ ሥራ አስተማሪው።

18. አሠሪው መንግሥት ከሆነ አላፊነት የሚኖርበት ሠራተኛው በቁጥር 2126/2/ እና 2127 በተደነገገው መሠረት "የሥራ ጥፋት" የፈፀመ እንደሆነ ብቻ ነው። አሠሪው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ወይም ግለሰብ ከሆነ አላፊ የሚሆነው ተቀጣሪው ሥራውን በማከናወን ላይ እያለ ለፈፀመው ጥፋት ነው። ቁጥር 2129 እና 2130ን ከቁጥር 2131 ጋራ አጣምር ይመልከቷል።

19. ቁጥር 2136ን እና ከላይ በማስታወሻ ቁጥር 1 የተጻፈውን ይመልከቷል።

20. ቁጥር 2072 እና 2082ን ይመልከቷል።

21. በማስታወሻ 2 እና 3 የተጻፈውን ይመልከቷል።

22. ከኸሞናዚች፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ይመልከቷል።

23. ቁጥር 2081ን ይመልከቷል።

24. ከሻሞኖሺች፣ አላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 51ን፣ የእርሳቸውን 145ኛ የግርጌ ማስታወሻና ገጽ 54ን ይመለከቷል።

25. የፈረንሳይኛው ቅጂ "ለሌሎች ሰዎች ተግባር አላፊ ስለመሆንና ስለብዙ ሰዎች አላፊነት" የሚል ይመስላል። እንደሚከተለውም ይነበባል፣ "De la responsiabilité du fait d'autrui et de la pluralité de responsables." የአማርኛው ቅጅ "ለሌላ ሰው <u>ተግባር</u> አላፊ ስለመሆን" ይላል /ሥርዝ የተጨመረ/። ስህተት መስሎ የሚታየው የፕሮፌሰር ከሺሞኖሺች የተሻሻለው ትርጉም ግን ዝምብሎ "ለሌሎች ሰዎች አላፊ ስለመሆን" ይላል።

26. ቁጥር 2136 እንደሚከተለው ይነበባል።
"/1/ አንድ ሰው ለአንድ ጉዳት በፍትሐብሄር በኩል አላፊ ነው ተብሎ በሕግ የተረጋገጠ መሆኑ ጉዳት አድራጊው ላደረሰው ጉዳት ካሣ መክፈልን አያስቀርለትም።

/2/ ጉዳት ያደረሰውና በፍትሐብሄር በኩል አላፊ የሆነው ለካሣው አከፋፈል የአንድነት ግዴታ አለባቸው።

/3/ በሕጉ አስተያየት ረገድ በፍትሐብሄር በኩል አላፊ ነው የተባለው በበኩሉ ጉዳት ያደረሰውን ዋንኛውን አላፊ በቀረበበት ክስ ውስጥ እንዲገባ ለማስገደድ ይችላል።"

27. ለጎል፣ አላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 5 ላይ ይመለከቷል።

28. ሌላው ዓላማ ብዙውን ጊዜ ካሣ የመክፈል አቅም የሌላቸው አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች በሚፈፅሟቸው የጥፋት ተግባሮች ጉዳት ለሚደርስባቸው ሰዎች

የካሣ ዋስትና ማስገኘት ነው። ፕሮፌሰር ክሽቼኖዊች እላይ በማስታወሻ ቁጥር 6 በተጠቀሰው መጽሐፋቸው በገጽ 54 ላይ ያሉትም ይህንኑ ነው። ሲናገሩም እነዚህ ሰዎች በሕግ መሠረት ዋስ ሲሆኑ፥ ዋስትናቸውም ልጁ ጥፋት እንዳይፈፅም ነው ብለዋል።

29. ለጉል፥ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ፥ ገጽ 5 ይመለከቷል።

30. ይህ መከላከያ ከአቅም በላይ ለሆኑ ምክንያቶች ብቻ እንዲያገለግል ተደርጎ አልተገደበም። የመቆጣጠር ተግባሩን በመፈፀም ረገድ ስሕተት ያልፈፀመ መሆኑን ለማሳየትም ማረጋገጫ ሊያቀርብ ይችላል። ላውሰን እላይ በማስታወሻ ቁጥር 4 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ከገጽ 227-228 ድረስ ይመለከቷል።

31. ቁጥር 635/1/።

32. ቁጥር 644/2/ በተጣማሪነት ከቁጥር 635/2/ ጋራ ሲነበብ።

33. የእናትዮዋ አላፊነት በአባትዮው አላፊነት ምትክ ከሆነ ደግሞ አባትዮው አላፊ በሆነበት ሁኔታ ልጁ በፈፀመው የጥፋት ተግባር ሳቢያ የመጣው ዕዳ የሚከፈለው ከአባትዮው የግል ሀብትና ይህ ካልበቃ ከጋራ ሀብታቸው ላይ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፥ ዕዳውን ለመክፈል የአባትዮው የግል ሀብትና የጋራ ሀብታቸው በቂ ሆኖ ካልተገኘ ዕዳው ከእናትዮዋ የግል ሀብት ላይ ሊከፈል አይችልም። አላፊነቱ የሚመለከተው እናትዮዋን በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ ሁኔታው የዚሁ ተገላቢጦሽ ይሆናል። ቁጥር 659ን በተጣማሪነት ከቁጥር 660 ጋራ ይመለከቷል።

34. ቁጥር 638

35. ቁጥር 681 በተጣጣሪነት ከቁጥር 682 ጋራ ሲነበብ

36. ቁጥር 639

37. ቁጥር 2125 /ለ/።

38. ቁጥር 2125 /ሐ/።

39. ሰነል፣ እላይ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰው መጽሐፍ ገጽ 23።

40. እዚያው በታ ይመለከቷል።

41. የእሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 64/68 አንቀጽ 27ን ይመለከቷል።

42. ያለጥፋት አላፊ በሚከንበት ሁኔታ እንደተደረገው ሳይሆን በዚህ ጉዳይ ይሀ መከላከያ እንዳያገለግል በግልፅ አልተከለከለም።

43. አንዳንድ አንባብያን አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ እንዴት በህጋዊ መንገድ የንብረት ባለሀብት ሊሆን ይችላል? በተለይም ደግሞ ጉዳት ሊያደርሱ አንድን ሰው ያለጥፋቱ አላፊ የሚያደርጉትን ንብረቶች እንዴት የግል ሀብቱ ሊያደርጋቸው ይችላል? ብለው ይጠይቁ ይሆናል። በእኛ ሕግ መሠረት አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ በባለሀብትነት ሊይዘው የሚችለውን የንብረት ዓይነት በሚመለከት ገደብ አልተደረገም። በመሆኑም አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ለንግድ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ወይንም ለሌሎች ሥራዎች አገልግሎት የተመደቡ የማናቸውም የንብረት ዓይነቶች ባለሀብት ሊሆን ይችላል። ቁጥር 288ን ይመለከቷል። አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ እነዚህን ንብረቶች በስጦታ፣ በኑዛዜ፣ ወይም በውርስ ሊያገኝ ይችላል። ቁጥር 287 እና 299 /1/ን ይመለከቷል። በነገራችን ላይ አካለመጠን ያላደረሰ ልጅ ሀብቶች ሁሉ በሞግዚት

እንደሚጠበቁና እንደሚተዳደሩ፣ እንዲሁም ሞግዚቱ የልጁ ንብረቶች ከራሱ የግል ንብረቶች ጋራ እንዳይደባለቁ ተገቢውን ማድረግ እንዳለበት መገንዘብ ያሻል። ቁጥር 280/2/ እና 283ን ይመለከቷል። ብዙውን ጊዜ አባትና እናት ጋብቻቸው ፀንቶ እስካለ ድረስ አካለመጠን ላላደረሱት ልጆቻቸው በአንድነት ሞግዚቶች ናቸው። ቁጥር 204ን ይመለከቷል።

44. እላይ በማስታወሻ ቁጥር 24 የተጠቀሰውን ይመለከቷል።

45. ክሽሞናሊች፣ በማስታወሻ ቁጥር 6 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 38 ይመለከቷል።

46. ሌጎል፣ በማስታወሻ ቁጥር 11 የተጠቀሰውን መጽሐፍ ገጽ 6 ይመለከቷል።